EVERY CHILD READY @Home

# ክፍል 9

## ምድራችን

PK3



AppleTree

# ክፍል 9
## ምድራችን

©2021
ሁሉም መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸዉ። በዚህ የቅጂ መብት ስር ከለላ የተደረገላቸዉን መብቶች ላይ ገደብ ሳያስቀምጥ፣ የዚህ ህትመት የትኛዉም አካል ማባዛት አይቻልም፣ ማከማቸት፣ ወይም በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚያዉል ስርዓት ዉስጥ ሊካተት አይችልም፣ ወይም በማንኛዉም መልክ ወይም ሁኔታ(ኤለክትሮኒክ፣ ሜካኒካል፣ ፎቶኮፒ፣ ድምጽ ቅጂ፣ ወይም ሌላ መንገድ) ቀደም ብሎ ከተሰጠ የጽሁፍ ፍቃድ ዉጪ ማስተላለፍ አይቻልም።

አፕል ትሪ ኢንቲቲዩት ፎር ኤዱኬሽን ኤኖቬሽን
1801 ሚሲሲፒ ጎዳና ኤስኢ፣ 3ኛ ፎቅ
ዋሽንግተን፣ ዲሲ 20020

የቅጂ መብት ©2021 ጽሁፍ እና የምስል ገለጻዎች። አፕል ትሪ ኢንስቲቲዩት። ሁሉም መብቶች በህግ የተጠበቁ ናቸዉ።

# PK3 ክፍል 9 ምልከታ



**ውድ ቤተሰቦች፡**

ወደ ክፍል 9፣ ምድራችን እንኳን በደህና መጣችሁ! በክፍል 9 ስር ልጆቻችሁ ምድራችንን ስለመሰረቷት እንደ መሬት፣ ውሀና አየር ስለመሳሰሉት ስለተለያዩ ነገሮች ይማራሉ።

## ክፍል 9 መጻህፍት



- Our Trip to the Farmers' Market /አወር ትሪፕ ቶ ዘ ፋርመርስ ማርኬት በ Felicia R. Truong
- Trash! /ትራሽ በ Katie Alexander
- The Inside of the Earth/ዘ ኢንሳይድ ኦፍ ዘ ኧርዝ በ Linda Gill
- Calvin the Cloud/ኬልቪን ዘ ክላውድ በ Mary Curley

*በተጨማሪም፣ ለሁሉም መጻህፍት ቀድመው የተቀዱ ንባቦች ለአዋቂዎች ጠቃሚ ምክሮች /Tips for Adults፣ ምድራችን/ Our Earth በሚለው ስር በሚገኘው Sparkler መተግበሪያ ላይ ማግኘት ይቻላል።*

***የECR የቤት ውስጥ ተግባሮች/ECR @Home activities ስለ ተፈጥሮ፣ ተክሎች፣ የውሀ ጥበቃ እና የውሀ ዑደት የተመለከተ ትምህርትን ይይዛሉ። ልጆቻችሁ ጥንድ ቃላትን ይመሰርታሉ፣ የቃላት ድምጽ ምቶችን ይለያሉ፣ እንዲሁም ስለ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው ይነጋገራሉ። ልጆቻችሁ በተጨማሪም ከ5-8 ቁጥሮችን ለይተው በያውቃሉ፣ መጠኖችን ያወዳድራሉ እንዲሁም እስከ 10 ቁሶችን ይቆጥራሉ። እነዚህን የትምህርት ተግባሮች በቤት ውስጥ ማስፋፋት የሚቻልባቸው የተለያዩ ዘዴዎች አሉ። ልጆቻችሁ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን መልሶ በመጠቀም እና አትክልትን ከወራጅ ውሀ ይልቅ በሳህን ውስጥ በማጠብ በውሀ ጥበቃ ላይ ሊያግዙ ይችላሉ።***

## ክፍል 9 ቃላት

- አየር
- ዳመና
- ጥበቃ
- ምድት
- ፈሳሽ
- ተክል
- ወቅት
- ጠጣር
- የአየር ሁኔታ



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሳምንት 1


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# PK3 ክፍል 9 ሳምንት 1 ምልከታ

## አየር፣ መሬት፣ ውሀና ምድራችን!

### በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥

በዚህ ሳምንት ልጅዎ ምድራችን መሬት፣ ውሀና አየር እንደምትይዝ ይማራል እንዲሁም የተፈጥሮ ቁሳቁሶችን ከሰው ሰራሽ ቁሳቁሶች ጋር ያወዳድራል። ልጅዎ በተጨማሪም የቃላት ምቶችን ይለያል፣ ጥንድ ቃላትን ይመሰርታል እንዲሁም እስከ 10 ቁሶችን ይቆጥራል። እነዚህን ተግባሮች በመኖሪያ መንደራችሁ ውስጥ የእግር ጉዞ በምታደርጉበት ወቅት የተፈጥሮ ቁሳቁሶችና ሰው ሰራሽ ቁሳቁሶችን ጠቁመው በማመልከት ማስፋፋት ይችላሉ።



### ቁልፍ ቃላት



**አየር**
በምድር ላይ የሚገኝ እና የምንተነፍሰው ጋዝ



**ምድር**
የምንኖርባት ፕላኔት


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት ስለምንኖርባት ምድራችን ይማራሉ። መርሀግብሩን ከመጀመርዎ በፊት ስለ ምድር በተመለከተ ማወቅ ስለሚፈልጉት ስለ አንድ ነገር በተመለከተ ይጻፉ እንዲሁም ይሳሉ።

ያስቡበት!


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

## **STEM:** ምን ያህል ቁሶች አሉ?

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ እንደ ጠጠሮች ወይም ማንኪያዎች የመሳሰሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶቸች፣ የእያንዳንዳቸው 10**

- ለልጅዎ 5 ማንኪያዎች ያሳዩት። ከዚያም **ምን ያክል ማንኪያዎች አሉ?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎ እርዳታ ካስፈለገው እያንዳንዱን ማንኪያዎች ጠቁመው እያሳዩት አብራችሁ ቁጠሩ።
- ሙከራውን ከ0 እስከ 10 መካከል ባሉ ቁጥሮች ከ2-3 ተጨማሪ ጊዜያት ደግማችሁ ስሩ። ልጅዎን መጨረሻ ላይ የሚጠው ቁጥር ጠቅላላ ድምሩ እንደሆነ እንዲረዳ ለመርዳት ከቆጠረ በኋላ ጠቅላላ ድምሩን ይንገሩት፣ ለምሳሌ፡ **5 ማንኪያዎች አሉህ!**
- ለልጅዎ ቁሶች እንዲያሳይዎና ቁሶቹን እንዲቆጥሯው እንዲጠይቅዎ ይፍቀዱለት።
- ልጅዎን ከመኖሪያ ቤታችሁ ዙሪያ ከ0-10 ቁሶች እንዲያመጣልዎ ይጠይቁት።

## በግል መማር፥ በመጫወቻ ሊጥ የሚሰሩ አበቦች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የመጫወቻ ሊጥ ወይም [በመጫወቻ ሊጥ የተዘጋጀ ምግብ]**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው በመኖሪያ ቤታችሁ ውስጥ ወይም ከመኖሪያ ቤታችሁ ውጭ አበቦችን ተመልከቱ ወይም ከታብሌት ወይም ስልክ ላይ የአበባ ስዕሎችን ተመልከቱ። ልጅዎን ከአበቦቹ ላይ ምን እንዳየ ይጠይቁት - የተለያዩ ቀለሞች፣ ቅርጾች፣ መጠኖች፣ ወዘተ።
- ልጅዎን በመጫወቻ ሊጥ አበቦችን እንዲሰራ ይፍቀዱለት።
- ልጅዎ በተጨማሪም እንደ ሶፍት፣ ወረቀት፣ ጥጥ (ዳንዴሊዮኖች ለመስራት)፣ ወዘተ በመሳሰሉ ሌሎች ቁሳቁሶች አበቦችን ሊሰራ ይችላል።


በመጫወቻ ሊጥ የሚደረግ የምግብ ዝግጅት

1 ኩባያ ዱቄት

2 የሻይ ማንኪያ የላመ ክሬም

1/3ኛ ኩባያ ጨው

1 ኩባያ ውሀ

1 የሻይ ማንኪያ የአትክልት ዘይት

የመረጡት አይነት የምግብ ማቅለሚያ

1. ዱቄቱን፣ የላመውን ክሬም እና ጨዉን የምግብ ማብሰያ ድስት ውስጥ ይክተቱ።
2. በምግብ ማብሰያ ድስቱ ውስጥ ውሀና የአትክልት ዘይት ይጨምሩ። ውህዱን በመካከለኛ/አነስተኛ ሙቀት ይቀላቅሉ።
3. ውህዱ መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ማቅለሚያውን ይጨምሩበት።
4. የድስቱ የስረኛው ክፍል ላይ እንዳይይዝ እና እንዳይጋገር ማማሰልዎን ይቀጥሉ።
5. ለጨዋታ ከማዋልዎ በፊት የመጫወቻ ሊጡ እንዲቀዘቅዝ ያድርጉ። ሊጡን አየር በማያስገባ መያዣ ውስጥ ያስቀምጡት።

PK3 የእንክብካቤ ማዕከል፡ ከቤት ቤተ እስከ ማንበብ — በመጫወቻ ሊጥ የምግብ ዝግጅት (FE)



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 9 ሳምንት 1 ቀን 1

## እውቀት፥ ጥንድ ቃላት

- ለልጅዎ **እስኪ ጥንድ ቃላትን እንመስርት!** ብለው ይንገሩት
- **እኔ ሁለት ቃላት እነግርሀለሁ። አንተ ቃላቱን አንድ ላይ በማድረግ አንድ ቃል ትመሰርታለህ** ይበሉት።
- **አዳምጥ: "night"** (ትንፋሽ ውሰድ) **"light"። ቃላቱን አንድ ቃል ማለትም night** (ትንፋሽ ውሰድ) **light፣ nightlight የሚለውን ቃል ለመመስረት አንድ ላይ አገናኛቸዋለሁ** ይበሉት።
- **ከዚያም አሁን ያንተ ተራ ነው። እነዚህን ሁለት ቃላት: "baket"** (ትንፋሽ ውሰድ) **"ball"፣ basket** (ትንፋሽ ውሰድ) **ball አንድ ቃል ለመመስረት አገናኝ** ብለው ይንገሩት። ልጅዎ እርዳታ ካስፈለገው ሁለቱን ቃላት አንድ ላይ ይናገሩና ጥንድ ቃሉን **Basket** (ትንፋሽ ውሰድ) **ball፣ አንድ ላይ basketball** ብለው ይንገሩት።
- ሙከራውን sailboat እና rainbow በሚሉት ቃላት ደግማችሁ ስሩ።

## *ያንብቡ፥ ወደ ገበሬዎች ገበያ የምናደርገው ጉዞ*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Our Trip to the Farmers' Market/ወደ ገበሬዎች ገበያ የምናደርገው ጉዞ*

- መጽሀፉን ከልጅዎ ጋር ሆነው መጽሀፉን ያንብቡ።
- ከዚያም **ትንሿ ልጅ መግዛት ስለምትችላቸው ስለ ሁሉም ነገሮች አስባለች። ከዚያም የሷንና የወንድ አያቷን ፎቶ የያዘ ስዕል ለመግዛት ወስናለች** ብለው ይንገሩት።
- **አንተ ምን ትመርጣለህ?** ብለው ይጠይቁት

በተጨማሪም የዚህን መጽሀፍ በቅድሚያ በድምጽ የተቀዳ ንባብ በSpakler መተግበሪያ ላይ "ለአዋቂዎች የቀረቡ ፍንጮች" ክፍል፣ ምድራችን ከሚለው ስር ማግኘት ይችላሉ።




አወር ትሪፕ ቱ ዘ
ፋርመርስ ማርኬት


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# በመጫወቻ ሊጥ የሚደረግ የምግብ ዝግጅት

1 ኩባያ ዱቄት

2 የሻይ ማንኪያ የላመ ክሬም

1/3ኛ ኩባያ ጨው

1 ኩባያ ውሀ

1 የሻይ ማንኪያ የአትክልት ዘይት

የመረጡት አይነት የምግብ ማቅለሚያ

1. ዱቄቱን፣ የላመውን ክሬም እና ጨዉን የምግብ ማብሰያ ድስት ውስጥ ይክተቱ።
2. በምግብ ማብሰያ ድስቱ ውስጥ ውሀና የአትክልት ዘይት ይጨምሩ። ውህዱን በመካከለኛ/አነስተኛ ሙቀት ይቀላቅሉ።
3. ውህዱ መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ማቅለሚያውን ይጨምሩበት።
4. የድስቱ የስረኛው ክፍል ላይ እንዳይይዝ እና እንዳይጋገር ማማሰልዎን ይቀጥሉ።
5. ለጨዋታ ከማዋልዎ በፊት የመጫወቻ ሊጡ እንዲቀዘቅዝ ያድርጉ። ሊጡን አየር በማያስገባ መያዣ ውስጥ ያስቀምጡት።






©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ



## STEM: ምድራችን፣ መሬት፣ አየር፣ ውሀ



**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ መሬት፣ አየር፣ ውሀ፣ ወረቀት፣ ከለሮች፣ የኩባያ ውሀ፣ ቆሻሻ ወይም ሳር (ወይም ስዕሎችን ከስልክ ወይም ታብሌት ላይ ያሳዩት)**

- ለልጅዎ **ስለምንኖርባት ምድራችን እየተማርን ነው። ምድር የተሰራችው ከአየር፣ መሬት እና ከውሀ ነው** ብለው ይንገሩት።
- ስለ እያንዳንዱ ለመንገር ስዕሎችና ቁሶችን ይጠቀሙ። **አየርን እንተነፍሰዋለን። አየርን አናየውም ሆኖም ለመኖር የሚያስፈልገንን ኦክስጂን ይይዛል** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም **ለመኖር ውሀ ያስፈልገናል። በውሀ ውስጥ ብዙ እንስሳት እና ተክሎች ይኖራሉ። ውሀ በተጨማሪም ሀይቆችን፣ ወንዞችና ውቂያኖሶችን ይይዛል** ይበሉት።
- ከዚያም **እኛ የምንኖረው መሬት ላይ ነው። መሬት ቆሻሻ፣ ሳርና ተራራዎች አሉት። መሬት ላይ ምን ተጨማሪ ነገሮች አሉ?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎን የመሬት፣ ውሀና አየር ስዕል እንዲስል ያድርጉ።

## በግል መማር፥ የቅጠል አርት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ውሀማ ቀለም ጥቅል፣ ማጣበቂያ፣ ከለሮች፣ ወረቀት፣ ቅጠሎች (ቅጠሎች ከሌሉዎ ልጅዎ ቅጠሎች ሊስል ወይም የቅጠል ቅርጽ በወረቀት ቆርጦ ሊሰራና ኮሌጅ ሊሰራ ይችላል)**

- ልጅዎን ቅጠሎችን በመጠቀም ምን አይነት አርት መስራት እንደሚፈልግ ይጠይቁት።
- ልጅዎ የሚከተሉትን ሊሰራ ይችላል:
  - ቅጠሎችን ቀለም ሊቀባና ወረቀት ላይ ሊያጣብቅ
  - የቅጠል ኮሌጅ ሊሰራ
  - የቅጠሎች ስዕሎች ሊስል
  - ቅጠል ሊፈገፍግ: ቅጠሎቹን ከወረቀት ስር አድርጎ ወረቀቱን በከለር መቀቢያ መፈተግ
- ከዚያም **ቅጠሎቹን እንዴት ተጠቀምክባቸው?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ



## እውቀት፥ ጤናማ አመጋገብ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** Healthy Eating/ጤናማ አመጋገብ


ጤናማ አመጋገብ

በኬቲ እና ቶሪ ፍሪትዝ

ለማደግ እና ሰውነታችሁን
ጠንካራ እንዲሆን ለማድረግ
እነዚህን ጤናማ የአመጋገብ ምክሮች ተከተሉ
ምንም ነገር አያገኛችሁም።

በርካታ ፍራፍሬዎችን እና አትክልቶችን
እንዲሁም ድፍን ስንዴ ተመገቡ።
የወተት ምርቶችን እና እንደ ስጋ እና ጥራጥሬ
ያሉ የፕሮቲን ምግቦችንም መርሳት የለባችሁም።

የሚቻላችሁን ሁሉ ካደረጋችሁ እና ምንም ነገር ካልረሳችሁ
ምናልባት ወላጆቻችሁ ማራኪ የሆነ አቀራረብ ያቀርቧችኋል።

- የቃላት ድምጽ ምትን ማዳመጥ ተለማመዱ። ለልጅዎ **የቃላት ድምጽ ምት መጨረሻቸው ተመሳሳይ ድምጽ ያላቸው ቃላት ናቸው፣ ለምሳሌ bee እና see። እስኪ ግጥም እናንብብና ምት ያላቸው ቃላትን እናዳምጥ** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም **መጨረሻቸው ተመሳሳይ ድምጽ ያላቸው አንዳንድ ቃላትን ሰምቻለሁ: strong, wrong** ይበሉት።
- ግጥሙን በዝግታ ደግመው ያንብቡ። ከዚያም **ምን ምት ያላቸው ቃላትን ትሰማለህ?** ብለው ይጠይቁት (strong-wrong፣ wheat-meat-beat-treat)። ምት ባላቸው ቃላት መጨረሻ ላይ አጽንኦት ይስጡ።
- ለመፈተን ልጅዎን ሌላ ምት ያላቸው ቃላትን እንዲነግርዎ ይጠይቁት። ቃሉ የተሰራ ቃል ሊሆን ይችላል!

## የጆርናል ሙከራ፥ ጉዞ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ እርሳስ፣ የጉዞ የጆርናል ገጽ**


ስም፥ ________________

በምድር፣ በአየር ወይስ በውሃ ላይ መጓዝ ትመርጣላችሁ?

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው መጓዝ ስለምትችሉባቸው ስለተለያዩ ዘዴዎች ተነጋገሩ- በየብስ፣ በአየር ወይም በውሀ።
- ልጅዎን ስለ መጓጓዣ ዘዴው እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ከዚያም **መጓዝ የምትፈልገው በየትኛው ዘዴ ነው - በየብስ፣ በአየር ወይስ በውሀ? ለምን?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።









©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ጤናማ አመጋገብ

በኬቲ እና ቶሪ ፍሪትዝ



ለማደግ እና ሰውነታችሁን

ጠንካራ እንዲሆን ለማድረግ

እነዚህን ጤናማ የአመጋገብ ምክሮች ተከተሉ

ምንም ነገር አያገኛችሁም።




በርካታ ፍራፍሬዎችን እና አትክልቶችን

እንዲሁም ድፍን ስንዴ ተመገቡ።

የወተት ምርቶችን እና እንደ ስጋ እና ጥራጥሬ

ያሉ የፕሮቲን ምግቦችንም መርሳት የለባችሁም።

የሚቻላችሁን ሁሉ ካደረጋችሁ እና ምንም ነገር ካልረሳችሁ

ምናልባት ወላጆቻችሁ ማራኪ የሆነ አቀራረብ ያቀርቧችኋል።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

በምድር፣ በአየር ወይስ በውሃ ላይ መጓዝ ትመርጣላችሁ?



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 9 ሳምንት 1 ቀን 3

## **STEM:** አበቦቹን መቁጠር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** Flower Sets/የተለያዩ አበባዎች፣ **ከለሮች, ደህንነቱ ለልጆች የማያሰጋ መቀስ**



- ልጅዎን **በዚህ ገጽ ላይ ስንት አበቦች እንዳሉ ቁጠር** ብለው ይንገሩት
- ከዚያም **አሁን አበቦቹን ቀለም መቀባት እና ቆርጠህ ማውጣት ትችላለህ** ይበሉት። አስፈላጊ ከሆነ ልጅዎን አበቦቹን ቆርጦ በማውጣት ላይ ይርዱት።
- ከዚያም የተለያየ መጠን ያላቸው አበቦችን ያስቀምጡ፣ ለምሳሌ፡ 4 አበቦች፣ ከዚያም 10 አበቦች እና ቀጥለውም ልጅዎን አበቦቹን እንዲቆጥራቸው ይንገሩት።

## በግል መማር፡ ተፈጥሮን መመልከት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** My Observations/ምልከታዎቼ, **ከለሮች፣ አለቶች፣ ቅጠሎች፣ ቀንበጦች፣ አበቦች የመሳሰሉ የተፈጥሮ ቁሳቁሶች**



- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ያሏችሁን የተፈጥሮ ቁሰቁሶች ግለጹ። ስለ መጠናቸው፣ ቅርጻቸው፣ ቀለማቸው እና ምን አይነት ስሜት እንደሚሰጡ ተነጋገሩ።
- ከዚያም **ምልከታህን መጻፍ ወይም መሳል ትችላለህ! በገጹ የላይኛው ጫፍ ላይ ስላየኸው ነገር ጻፍ። በገጹ የመካከል ክፍል ላይ ምን አይነት ስሜት እንደሰጡህ ጻፍ። በገጹ የስረኛው ክፍል ላይ ደግሞ ምን አይነት ሽታ እንዳላቸው ጻፍ** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ ተግባሩን እንዲያጠናቅቅ ይፍቀዱለት።
- ከዚያም **ምን ተመለከትክ?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## እውቀት፥ አስመስሎ መተወን

- ለልጅዎ **አንድ ቃል እነግርሀለሁ። ቃሉ ምን ማለት እንደሆነ አስመስለን መተወን እንችላለን** ብለው ይንገሩት።
- ከጭብጥ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቃላት ይጠቀሙ፤ ምሳ፡ አበባ (ልክ እንደ አበባ አስመስላችሁ ማደግና መፍካት ትችላላችሁ)፣ አየር (ለመተንፈስ ወይም ለመብረር አስመስላችሁ ሞክሩ)፣ የገበሬ ገበያ (የሆነ ነገር የምታዩና የምትገዙ አስመስሉ)።
- ልጅዎ ለእርስዎ ቃል መንገር እንዲችል ሚናችሁን ተቀያየሩ።

## ያንብቡ፥ ወደ ገበሬዎች ገበያ የምናደርገው ጉዞ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Our Trip to the Farmers' Market/አወር ትሪፕ ቱ ዘ ፋርመርስ ማርኬት*

- መጽሀፉን ከልጅዎ ጋር አብራችሁ አንብቡ።
- ከዚያም **እስኪ ወደ ገበሬዎች ገበያ ወይም መደብር/ገበያ ስለሄድክበት ጊዜ ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎን ስላጋጠሙት ስለ 2 ነገሮች እንዲነግርዎ ያበረታቱት፤ ምሳ፡ በመጀመሪያ የተወሰነ መጨናነቅ ያጋጥመናል፣ ከዚያም ለእያንዳንዱ ነገር እንከፍላለን።
- ልጅዎን ለመርዳት ጥያቄዎች ሊጠይቁት ይችላሉ፤ ምሳ፡ በተጨማሪ ምን አደረግክ?




አወር ትሪፕ ቱ ዘ
ፋርመርስ ማርኬት


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 9 ሳምንት 1 ቀን 3

## እስኪ እንንቀሳቀስ፥ አየር፣ መሬት፣ ውሀ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** Air, Land, Water/አየር፣ መሬት፣ ውሀ፣
**ማጣበቂያ**

- ካርዶችን ወለል ላይ አራርቀው ያጣብቁ ወይም ያስቀምጡ።
- ከዚያም **የሆነን ነገር ስም እጠራልሀለሁ። ከዚያም የጠራሁልህን ነገር ማግኘት ወደምትችልበት ስዕል ትሄዳለህ - አየር ላይ፣ ውሀ ወይም መሬት ላይ። በምትፈልገው መልኩ መንቀሰቀስ ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- እንደ ደመና፣ አሳ፣ የጭነት መኪናዎች፣ ጀልባዎች፣ አውሮፕላኖች፣ ጭልፊቶች፣ ወዘተ የመሳሰሉ ቃላትን ይናገሩ።
- ሚናችሁን ተቀያየሩና ልጅዎ እንዲመራዎ ይፍቀዱለት።



## በጋራ መማር፥ ታሪካችን

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ **እስኪ አንድ ላይ ሆነን ታሪክ እንናገር። እስኪ በዚህ ሳምንት ስላጋጠሙን ስለ ሁለት ነገሮች እንነጋገር** ብለው ይንገሩት።
- **ተሪኩ ስለ እኛ የተመለከተ ስለሆነ እኛ የታሪኩ ገጸ ባህሪያት እንሆናለን። ይህ የተከሰተው የት ነበር? ቦታው የታሪኩ መቼት ነው** ይበሉት።
- ልጅዎን ሁለት ክስተቶችን የሚይዝ ታሪክ እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ፤ ምሳ፡ ሁለታችሁም ወደ ገበያ ማዕከል ትሄዱና በመንገዳችሁ ላይ ትንሽ የቤት ውሻ ታያላችሁ። ከዚያም ስለ ታሪኩ በጋራ ተነጋገሩበት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# የእኔ ምልከታዎች



ስም፥ ____________________

ተግባር፥ ____________________








©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 9 ሳምንት 1 ቀን 4

## STEM: ተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ከለሮች፣ ወረቀት፣ አለቶች፣ ቅጠሎች ወይም ቀንበጦች የመሳሰሉ የተፈጥሮ ቁሳቁሶች፣ እና አሻንጉሊቶች ወይም የእቃ መያዣዎች የመሳሰሉ ሰው ሰራሽ ቁሳቁሶች**

- ለልጅዎ **ይህ ___ የተፈጥሮ አካል ነው። ተፈጥሮ እንደ ተክሎች፣ እንስሳት፣ የአየር ጸባይ፣ ቆሻሻና አለቶች የመሳሰሉ ነገሮች ናቸው። ሰዎች እነዚህን ነገሮች መፍጠር አይችሉም** ብለው ይንገሩት።
- የተወሰነ ሰው ሰራሽ ነገሮች ያሳዩት። **ይህ ___ በሰዎች የተሰራ ነው። ይህ ሰው ሰራሽ ነው** ብለው ይንገሩት።
- በወረቀት መካከል ላይ ወደ ታች መስመር ይሳሉና አንደኛውን ጎን "የተፈጥሮ" እና ሌላኛውን ጎን "ሰው ሰራሽ" ብለው ምልክት ይስጡት። ከዚያም **እስኪ የተለያዩ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ነገሮችን እንዘርዝር** ብለው ይንገሩት።
- በተጨማሪም የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቁሶች ስዕሎችን መጠቀም ይችላሉ።

## በግል መማር፡ የአየር፣ መሬት፣ ውሀ መገጣጠም

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** [Air, Land, Water Puzzle/የአየር፣ መሬት፣ ውሀ መገጣጠም፣](#) **ከለሮች፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀሶች፣ *በአማራጭነት - ቁርጥራጮችን ተቆርጠው ከመውጣታቸው በፊት ካርቶን ላይ በማጣበቂያ ማጣበቅ***



- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለ ስዕሉ እና በመሬት፣ አየር እና በውሀ ውስጥ ስለሚያያቸው ነገሮች ተነጋገሩ።
- ልጅዎ ስዕሎቹን ቀለም ከቀባ በኋላ ቁርጥራጮችን ቆርጦ እንዲያወጣና ወደ ሙሉ ስዕል እንዲገጣጥማቸው ይርዱት።
- ከዚያም **መሬት ላይ ምን ተጨማሪ ነገሮችን ታገኛለህ?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ



## እውቀት፥ እስኪ ስለ ምድራችን እንነጋገር

- ልጅዎን **ስለ ምድር እና በመሬት፣ አየር ላይ እና ውሀ ውስጥ ስለምናገኛቸው ነገሮች እየተማርን ነው። በውሀ ውስጥ መኖር ምን የሚመስል ይመስልሀል?** ብለው ይጠይቁት
- ከዚያም ልጅዎን ከ2-3 የክትትል ጥያቄዎችን ይጠይቁት። **በውሀ ውስጥ መኖር ትመርጣለህ ወይስ መሬት ላይ መኖር ትመርጣለህ? ለምን?** ወይም **አየር ላይ መኖር ትመርጣለህ? ለምን?** ብለው ይጠይቁት። የሀሳብ ልውውጥ ውይይት ለማድረግ ሞክሩ።
- ልጅዎ ስለዚህ ርዕሰ ጉዳይ መነጋገር የማይፈልግ ከሆነ በዚህ ምትክ ስለ ምን ጉዳይ መነጋገር ትመርጣለህ ብለው ይጠይቁት።

## የጆርናል ሙከራ፥ የት መኖር ትፈልግ ነበር?

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ እርሳስ፣ የየት መኖር ትፈልግ ነበር የጆርናል ገጽ**


ስም፥ ____________________

በምድርን ላይ በፈለጉት ቦታ የመኖር እድሉ ቢኖሮዎት መኖር የሚፈልጉት የት ነው?

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ሁለታችሁም መኖር ስለምትፈልጉባቸው ስለተለያዩ ቦታዎች ተነጋገሩ።
- ልጅዎን ስለዚህ እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ
- ከዚያም **ይህን ቦታ ለምን መረጥከው?** ብለው ይጠይቁት


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፡ ________________

በምድርን ላይ በፈለጉት ቦታ የመኖር እድሉ ቢኖሮዎት መኖር የሚፈልጉት የት ነው?


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ



## **STEM:** ትልቅ ወይም ትንሽ?

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የተለያዩ መጠኖች ያሏቸው ቁሶች፣ ወረቀት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ 2 የተለያየ መጠን ያላቸው ቁሶች ያሳዩት እና **ከሁለቱ ትልቁ የትኛው ነው?** ብለው ይጠይቁት
- 2 ሌሎች ቁሶች ያሳዩትና **ይሄኛው ከሌላኛው ይተልቃል ወይስ ያንሳል?** ብለው ይጠይቁት
- ቀጥለውም **እስኪ ክብ ሳልልኝ። ትንሽ ክብ ሳልልኝ። አሁን ደግሞ በመጠኑ ከመጀመሪያው ትልቅ የሆነ ክብ ሳልልኝ** ብለው ይጠይቁት።
- ከዚያም **እስኪ ተነስተን እንቁም እና እራሳችንን ትልቅ ለማድረግ እንዘረጋጋ። እራሳችንን እንዴት ማሳነስ እንችላለን?** ብለው ይጠይቁት።
- ለመፈተን ልጅዎን 3 ቁሶችን በመጠን እንዲያስቀምጣቸው ይጠይቁት እና ከመካከላቸው ትልቁ እና ትንሹ የትኛው ነው ብለው ይጠይቁት።

## በግል መማር፥ የክሎሮፊል ስዕሎች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** Tree Outline/የዛፍ ስዕል፣ **ቅጠሎች ወይም የጎመን ቅጠሎች፣ የብረት ማንኪያ**

- ለልጅዎ **ክሎሮፊል ለተክል ቅጠሎች አረንጓዴ ቀለም እንዲያገኙ የሚያደርጋቸው እና የጸሀይ ብርሀንን ወደ ምግብነት እና እኛ ወደምንተነፍሰው አየር እንዲቀይሩ የሚያስችላቸው ነገር ነው** ብለው ይንገሩት።
- **አሁን ደግሞ በክሎሮፊል አርት ለመስራት እንዲያስችለን ቅጠሎችን እንደራርባቸዋለን** ይበሉት። የዛፍ ስዕል ወረቀቱን ቅጠሎቹን በውስጥ በኩል በማድረግ እንዴት ግማሽ ላይ እንደሚታጠፍ በምሳሌ ያሳዩት። ከዚያም ከዚያም የብረት ማንኪያውን ከውስጥ በኩል ቅጠሎችን የያዘውን ወረቀት ወደ ውስጥ ለመብሳት ይጠቀሙበት።
- ለልጅዎ ቅጠሎቹን በማንኪያው እንዲበሳ ወይም ቅጠሎቹን በመሰባበር ወይም በመጠቀለል እና በቀጥታ ወረቀት ላይ ተጭኖ በመያዝ፣ ወዘተ ሙከራ እንዲሰራ ይፍቀዱለት።
- ቅጠሎች ከሌሉዎ ልጅዎ ስዕል ሊቀባ ይችላል።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ

PK4 Unit 9 Week 1 Day 5

## እውቀት፥ ግብ ምንድን ነው?

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Our Trip to the Farmers' Market/አወር ትሪፕ ቱ ዘ ፋርመርስ ማርኬት*




- ልጅዎን **ግብ ምነድን ነው?** ብለው ይጠይቁት እና **ግብ የምንፈልገው ወይም ለማግኘት ወይም ለማድረግ የምንፈልገው ነገር ነው። የታሪክ ገጸ ባህሪያትም ግብ ሊኖራቸው ይችላል** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም **ይህን መጽሀፍ ሳነብልህ የገጸ ባህሪውን ግብ ፈልገህ ለማግኘት አዳምጥ** ይበሉት።

- *ደ ገበሬዎች ገበያ የምናደርገው ጉዞ/ Our Trip to the Farmers' Market* መጽሀፍን ገጽ 8-9 ያንብቡለት። ከዚያም **የልጃገረዷ ግግ ምን ነበር? አዎ፤ ልጂቷ የምትገዛውን ነገር መምረጥ ትፈልግ ነበር** ብለው ይንገሩት።
- ልጂቷ ለግቧ እንዲረዳት ምን ታደርግ ነበር? **አዎ፤ ለመወሰን እንዲረዳት የወደደቻቸውን ነገሮች ስዕሎች ትወስድ ነበር** ብለው ይንገሩት።

## *ያንብቡ፥ ወደ ገበሬዎች ገበያ የምናደርገው ጉዞ*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Our Trip to the Farmers' Market/አወር ትሪፕ ቱ ዘ ፋርመርስ ማርኬት*

- መጽሀፉን ከማንበባችሁ በፊት ለልጅዎ **መጽሀፉን ሳነብልህ ከተክሎች የሚገኙ ሁሉንም ምግቦች ትፈልጋለህ** ብለው ይንገሩት። አንድ ላይ ሆናችሁ እንደ ፍራፍሬዎች፣ አትክልት፣ መርማራታና ማር የመሳሰሉ ከተክሎች ወይም ከተክል ተዋጽዎች የምናገኛቸውን ነገሮች ለይታችሁ አውጡ።
- ከዚያም **ለመመገብ የምትወደው ከተክሎች የሚገኝ ነገር ምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት




አወር ትሪፕ ቱ ዘ ፋርመርስ ማርኬት


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሳምንት 2


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# PK3 ክፍል 9 ሳምንት 2 ምልከታ

## የውሀ ጥበቃ



### በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥

በዚህ ሳምንት ልጅዎ ስለ ውሀ ጥበቃ እና ቆሻሻን ስለመቀነስ፣ ድጋሚ ስለመጠቀምና መልሶ ጥቅም ላይ ስለማዋል በተመለከተ ይማራል። ልጅዎ 10 ቁሶችን ይቆጠራል፣ ጥንድ ቃላትን ይመሰርታል እንዲሁም ስለ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው በተመለከተ ይነጋገራል። እነዚህን ተግባሮች ቆሻሻን በመቀነሻ፣ ድጋሚ መጠቀሚያና መልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ተግባሮች ላይ በመሳተፍ ማስፋፋት ይችላሉ።

### ቁልፍ ቃላት



**ጥበቃ**

ተክሎች እና እንስሳት እንዳይጠፉ ለማድረግ የሚደረግ መከላከል



**ፈሳሽ**

ጠጣር ወይም ጋዝ ያልሆነ ነገር



**ጠጣር**

የተወሰነ ቅርጽ ያለው ነገር

**PK3 ምድራችን**

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት ቆሻሻዎች ከተጣሉ በኋላ ወዴት እንደሚሄዱ ይማራሉ። መርሀግብሩን ከመጀመርዎ በፊት ቆሻሻ ወዴት እንደሚሄድ በተመለከተ የሚያስቡትን ነገር ይሳሉ እንዲሁም ይጻፉ።

**ያስቡበት!**


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## STEM: ረጅም ወይም አጭር?

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የተለያየ ቁመት ያላቸው ቁሶች፣ ወረቀት፣ ከለሮች**

- የተለያየ ቁመት ያላቸው 2 ቁሶች ያሳዩትና **አጭሩ የትኛው ነው?** ብለው ይጠይቁት።
- ሌሎች 2 ቁሶች ያሳዩት እና **ይሄኛው ከሌላኛው አጭር ነው ወይስ ረጅም ነው?** ብለው ይጠይቁት።
- ከዚያም **እስኪ የማማ ስዕል ሳል። ከዚህ ማማ በቁመት የሚያንስ ማማ ሳል። አሁን ደግሞ በቁመት ከመጀመሪያው ማማ የሚበልጥ ማማ ሳል** ብለው ይጠይቁት።
- ቀጥለውም **እስኪ ራሳችንን አጭር ለማድረግ እናጎንብስ። እንዴት ራሳችንን ረጅም ማድረግ እንችላለን?** ብለው ይጠይቁት።
- ለመፈተን ልጅዎን 3 ቁሶችን በመጠናቸው እንዲያስቀምጥ ይጠይቁት እና የትኛው አጭር እና የትኛው ረጅም እንደሆነ እንዲነግርዎ ይጠይቁት።

## በግል መማር፥ የውሀ ጨዋታ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ትልቅ የማያፈስ የውሀ መያዣ፣ ውሀ የያዘ ባልዲ ወይም የመታጠቢያ ቤት ገንዳ፣ መንሳፈፍ የሚችሉ ቁሶች፤ ምሳ፡ የጠርሙስ ክዳኖች፣ ቅጠሎች፣ ቀጫጭን ዱላዎች፣ *በአማራጭነት - በውሀው ውስጥ ሰማያዊ የምግብ ማቅለሚያ መጨመር***

- ለልጅዎ **በውሀ እየተጫወትክ ልትዝናና ትችላለህ** ብለው ይንገሩት። ልጅዎን በቁሶች መጠቀም ምን ያክል እንደሚወድ ይጠይቁት፤ ምሳ፡ የጠርሙስ ክዳኖችን እንደ ጀልባ ወይም ቅጠሎችን እንደ አሳ
- ልጅዎ ከተጫወተ በኋላ **በውሀ ውስጥ መጫወት ምን ያክል ትወዳለህ?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎን ውሀን መልሶ ስለመጠቀም እንዲማር ለማስቻል ውሀውን አትክልት ለማጠጣት ወይም ሳህን ለማጠብ በድጋሚ ተጠቀሙ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 9 ሳምንት 2 ቀን 6

## እውቀት፥ ችግር

- ልጅዎን **ችግር የሆነ ነገር ሲሳሳት ነው። ስላጋጠመህ ችግር ልትነግረኝ ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት
- ከልጅዎ ጋር ስለ ችግሩ ወይም ስለ ቤተሰባችሁ ችግር ይነጋገሩ፤ ምሳ፡ የአንዳንድ የቤተሰብ አባላት መደበኛ ተግባሮቻቸውን ሳይሰሩ መርሳት። ችግር ማለት ምን እንደሆነ ተነጋገሩ፤ ምሳ፡ ሰዎች ስራቸውን የማይሰሩ ከሆነ መኖሪያ ቤት ንጽህናው ላይጠበቅ ይችላል።
- መፍትሄ ይዛችሁ ቅረቡ፤ ምሳ፡ ሰዎች የሚወዱትን ስራ መስራት እንዲችሉ መደበኛ ተግባሮችን ማስመረጥ።

## ያንብቡ፥ ቆሻሻ/ትራሽ!

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Trash/ቆሻሻ!*

- ከልጅዎ ጋር ሆነው መጽሀፉን ያንበብቡ።
- ከዚያም የብዙ ቆሻሻ መኖር ስለሚያስከትላቸው ውጤቶች ተነጋገሩ። ለልጅዎ **ብዙ ነገሮችን የምንጥል ከሆነ በቆሻሻ ጉድጓዳችን ወይም ቆሻሻ መጣያችን ውስጥ ብዙ ቆሻሻ ስለሚጠራቀም ይህ ለምድራችን ጥሩ አይሆንም** ብለው ይንገሩት።

በተጨማሪም፣ ለሁሉም መጻህፍት ቀድመው የተቀዱ ንባቦች ለአዋቂዎች ጠቃሚ ምክሮች /Tips for Adults፣ ምድራችን/ Our Earth በሚለው ስር በሚገኘው Sparkler መተግበሪያ ላይ ማግኘት ይቻላል

ትራሽ!




ደራሲ፥ በኬቲ አሌክሳንደር
ሰዓሊ፥ በአሌክስ ሳቭቹክ


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 9 ሳምንት 2 ቀን 7

## STEM: ውሀ መቆጠብ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ **ምድራችንን መርዳት ከምንችልባቸው ዘዴዎች መካከል አንዱ የውሀ ቁጠባና ጥበቃ ነው። ብዙ ውሀ በመጠቀም ውሀን ማባከን የለብንም** ብለው ይንገሩት።
- አንድ ላይ ሆናችሁ ውሀን መቆጠብ ስለሚቻልባቸው ዘዴዎች ተነጋገሩ፤ ለምሳሌ፡ ጥርሳችንን በምንፍቅበት ወይም በመታጠቢያ ገንዳ ወይም ሻወር ውስጥ ሳሙና በምንመታበት ወቅት የቧንቧ መክፈቻውን መዝጋት። በተጨማሪም አጭር ሻወር መውሰድ እና አትክልትና ፍራፍሬዎችን በወራጅ ውሀ ከማጠብ ይልቅ በሳህን ውስጥ ማጠብ።
- ለልጅዎ በቤት ውስጥ ውሀን መቆጠብ የሚቻልባቸውን ዘዴዎች የሚያሳይ ፖስተር እንዲሰራና እንዲለጥፈው ይፍቀዱለት። ከዚያም **አንዱ ዛሬ መሞከር የምንችለው ውሀን መቆጠብ የምንችልበት ዘዴ ምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።

## በግል መማር፥ ከተጣሉ ነገሮች የሚሰሩ ፍሬሞች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ውሀማ ቀለም ጥቅል፣ ወረቀት፣ ማጣበቂያ፣ መቀሶች፣ ካርቶን፣ ምሳ፡ የስዕል ፍሬም እንዲመስል ተደርጎ የተቆረጠ የጥራጥሬ ሳጥን ወይም ፍሬም ለመስራት አንድ ላይ የታሰሩ ቀጫጭን ዱላዎች፣ እንደ ቅጠሎች፣ ልብስ ወይም የወረቀት ሽንተረሮች የመሳሰሉ የማስዋቢያ ቁሳቁሶች**

- ለልጅዎ **ነገሮችን መልሰን የምንጠቀምበት አንደኛው ዘዴ ሌላ አዲስ ነገር ከመግዛት ይልቅ ቁሶቹን ይህን ነገር ለመስራት መልሰን መጠቀም ነው። ነገሮችን የስዕል ፍሬም ለመስራት መልሰን መጠቀም እንችላለን** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን የራሱን ፍሬም እንዲሰራ ይፍቀዱለት።
- ከዚያም **እነዚህን ቁሶች በድጋሚ የተጠቀምክባቸው እንዴት ነው?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎ በፍሬሙ ውስጥ የሚያስቀምጠውን ስዕል ሊስል ወይም ሊመርጥ ይችላል።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ



## እውቀት፥ እስኪ የቃላት ምት/ቅላጼ እንስራ!

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Trash/ትራሽ!*

- ምት ያላቸው ቃላትን ማዳመጥ ተለማመዱ። ለልጅዎ **ምት ያላቸው ቃላት መጨረሻ ላይ ተመሳሳይ ድምጽ ይሰጣሉ፤ ለምሳሌ: snap እና clap። እስኪ እነዚህን ገጾች እያነበብን ምት ያላቸው ቃላትን እናዳምጥ** ብለው ይንገሩት።
- ገጽ 6-7ን ያንብቡለት እና **መጨረሻ ላይ ተመሳሳይ ድምጽ ያላቸው የተወሰኑ ምት ያላቸው ቃላትን ሰምቻለሁ: road, load** ይበሉት።
- ገጾቹን በዝግታ መልሰው ያንብቡ። ከዚያም **ምን ምት ያላቸው ቃላትን ትሰማለህ?** (road-load, scene-clean) ብለው ይጠይቁት። ምት ባላቸው ቃላት መጨረሻ ላይ አጽንኦት ይስጡ።
- ለመፈተን ልጅዎን ሌሎች ምት ያላቸው ቃላትን እንዲነግርዎ ይጠይቁት። ቃላቱ የተፈጠሩ ሊሆኑ ይችላሉ!

ብዙ ቆሻሻ ሲኖረን ቆሻሻውን መንገድ ዳር ባለው መጣያ ውስጥ እንጥላለን




ከዛም ቆሻሻ የሚሰበስበው መኪና ይመጣና ቆሻሻውን ይዞት ይሄዳል

## የጆርናል ሙከራ፥ ውሀን እንዴት እንደምጠቀም

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ እርሳስ፣ የውሀን እንዴት እንደምጠቀም የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ውሀን ስለሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ተነጋገሩ፤ ለምሳሌ፡ ምግብ ለማብሰል፣ ለመጠጣት፣ ተክሎችን ለማጠጣት፣ ለሰውነት መታጠቢያ ወይም እጆቹን ለመታጠብ
- ልጅዎን ስለሚጠቀምበት ዘዴ እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ
- ከዚያም **ውሀን እንዴት እንደምትጠቀም ንገረኝ?** ብለው ይጠይቁት


ስም፥ ________________

ውሃን የምጥተቀሙት በምን አይነት መንገድ ነው?


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

ውሃን የምጥተቀሙት በምን አይነት መንገድ ነው?


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 9 ሳምንት 2 ቀን 8

## **STEM:** ስንት ጣቶች አሉ?

- 6 ጣቶችዎን ወደ ላይ ያውጡና **ወደ ላይ ያነሳሁት ምን ያክል ጣቶቼን ነው?** ብለው ይጠይቁት። ለልጅዎ ጣቶችዎን እንዲቆጥር ይፍቀዱለት። ከዚያም ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው ጣቶቹን ወደ ላይ እንዲያነሳ ያድርጉት።
- ሙከራውን በ0 (በመጀመሪያ የርስዎን ያሳዩት) እና 10 መካከል ባሉ ቁጥሮች ከ3-4 በተጨማሪ ጊዜያት ደግማችሁ ስሩ።
- በጣቶች መቁጠር ለልጅዎ በኋላ ላይ ለሂሳብ ስሌቶችና የችግር አፈታት ይረዳዋል።

## በግል መማር፥ የውሀ ምንጮች መገጣጠም

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** Water Sources Puzzle/የውሀ ምንጮች መገጣጠም፣ **ለሀጻናት ተስማሚ መቀሶች፣ ከለሮች፣** ***በአማራጭነት - ቁርጥራጮቹን ቆርጠው ከማውጣትዎ በፊት ካርቶን ላይ ያጣብቋቸው***



- ለልጅዎ ውሀ ማግኘት የሚችልባቸው የተለያዩ ቦታዎችን ለመንገር ስዕሉን ይጠቀሙ፤ ምሳሌ፡ ዝናብ፣ ወንዞችና ሀይቆች
- ከዚያም **ስዕሎቹን ቀለም መቀባትና ከዚያም ቆርጠን እናወጣና አንተ ልትገጣጥመማቸው ትችላለህ** ይበሉት።
- ለልጅዎ ቁርጥራጮቹን እራሱን ችሎ ቀለም እንዲቀባና እንዲገጣጥማቸው ይፍቀዱለት። አስፈላጊ ከሆነ ቆርጦ በማውጣት ላይ ይርዱት።
- ከዚያም **በቤት ውስጥ ውሀ የት ታገኛለህ?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

## እውቀት፥ ጥንድ ቃላት

- ለልጅዎ **እስኪ ጥንድ ቃላትን እንመስርት! እኔ ሁለት ቃላት እነግርሀለሁ። አንተ ደግሞ አንድ ቃል ለመፍጠር ቃላቱን አንድ ላይ ታገናኛቸዋለህ** ብለው ይንገሩት።
- **አዳምጥ: " dog "** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **" house "። ቃላቱን አንድ ቃል ማለትም dog** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **house፣ doghouse. የሚለውን ቃል ለመመስረት አንድ ላይ አገናኛቸዋለሁ** ይበሉት።
- **ከዚያም አሁን ያንተ ተራ ነው። እነዚህን ሁለት ቃላት: " sun "** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **" shine "፣ sun** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **shine አንድ ቃል ለመመስረት አገናኝ** ብለው ይንገሩት። ልጅዎ እርዳታ ካስፈለገው ሁለቱን ቃላት አንድ ላይ ይናገሩና ጥንድ ቃሉን ይንገሩት። **በጥንቃቄ አስበው! Sun** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **shine፣ አንድ ላይ ሲገናኙ sunshine ይሆናል** ይበሉት።
- ሙከራውን airport እና playpen በሚሉት ቃላት ደግማችሁ ስሩ።

## ያንብቡ፥ *Trash/ትራሽ!*

ትራሽ!

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Trash/ትራሽ!*

- መጽሀፉን ከልጅዎ ጋር ሆነው ያንብቡ።
- ከዚያም እንዴት ቆሻሻን መቀነስ እንደሚችሉ ተነጋገሩ፤ ምሳ: ጥቂት መጠቅለያዎች ያላቸው ነገሮችን መግዛት ወይም ከፕላስቲክ ከረጢቶች ይልቅ ቦርሳዎችን መጠቀም። አንድ ላይ ሆናችሁ ዝርዝር ጻፉና ለልጅዎ ዝርዝሩን እንደ ማስታወሻ እንዲያገለግለው የሆነ ቦታ እንዲያስቀምጠው ይፍቀዱለት።




ደራሲ፥ በኬቲ አሌክሳንደር
ሰዓሊ፥ በአሌክስ ሳቭቹክ


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## እስኪ እንንቀሳቀስ፥ ቆሻሻ መወርወር/ማስወገድ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ኳስ ወይም ከካልሲ የተሰራ ኳስ፣ የእቃ መያዣ ወይም ሳጥን**

- ለልጅዎ **እስኪ ቆሻሻችንን ስለመወርወር እንለማመድ! ኳሱን ቆሻሻ እና የእቃ መያዣውን የቆሻሻ መጣያ እንደሆነ አስመስለን እንስራ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎ ኳሱን ለምን ያክል ተከታታይ ጊዜ የእቃ መያዣው ውስጥ እንደጨመረ ሊቆጥር ይችላል ወይም ብዙ ኳሶች ሊጠቀምና ድምራቸውን መጨረሻ ላይ በእቃ መያዣው ውስጥ ሊቆጥር ይችላል።

## በጋራ መማር፥ ምድራችንን መገንባት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የመጨዋቻ ሊጥ ወይም [የመጨዋቻ ሊጥ አሰራር]፣ ወይም እንደ የወረቀት ጥቅሎች፣ የእቃ መያዣዎች፣ የተጨማደደ ወረቀት፣ ውሀማ ቀለም ጥቅል፣ ወዘተ የመሳሰሉ በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶች**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የምድር ወይም የተወሰነ ቦታ ስዕሎችን ከስልክዎ ወይም ታብሌትዎ ላይ ተመልከቱ። እንደ አህጉሮች እና ውቂያኖሶች የመሳሰሉ ባህሪያትን ለይተው ያውጡ።
- ከዚያም **እስኪ አንድ ላይ ሆነን ምድርን እንገንባ** ይበሉት። በጋራ የምትወስኗቸው የተለያዩ ባህሪያትን ለመስራት ቁሳቁሶችን ተጠቀሙ።


በመጫወቻ ሊጥ የሚደረግ የምግብ ዝግጅት

1 ኩባያ ዱቄት

2 የሻይ ማንኪያ የላመ ክሬም

1/3ኛ ኩባያ ጨው

1 ኩባያ ውሀ

1 የሻይ ማንኪያ የአትክልት ዘይት

የመረጡት አይነት የምግብ ማቅለሚያ

1. ዱቄቱን፣ የላመውን ክሬም እና ጨዉን የምግብ ማብሰያ ድስት ውስጥ ይክተቱ።
2. በምግብ ማብሰያ ድስቱ ውስጥ ውሀና የአትክልት ዘይት ይጨምሩ። ውህዱን በመካከለኛ/አነስተኛ ሙቀት ይቀላቅሉ።
3. ውህዱ መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ማቅለሚያውን ይጨምሩበት።
4. የድስቱ የስረኛው ክፍል ላይ እንዳይይዝ እና እንዳይጋገር ማማሰልዎን ይቀጥሉ።
5. ለጨዋታ ከማዋልዎ በፊት የመጫወቻ ሊጡ እንዲቀዘቅዝ ያድርጉ። ሊጡን አየር በማያስገባ መያዣ ውስጥ ያስቀምጡት።

በመጨዋቻ ሊጥ የምግብ ዝግጅት (FE)


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 9 ሳምንት 2 ቀን 9

## **STEM:** ጠጣር ነገሮችና ፈሳሾች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፦ ውሀ፣ የበረዶ ኩብ**

- ለልጅዎ **እስኪ በጠጣር ነገሮችና ፈሳሾች ላይ ምርምር እንስራ። ጠጣር ነገር እንደ ወንበር ያለ ቅርጹን የማይቀይር ነገር ነው። ፈሳሽ ደግሞ የሚፈስና ቅርጹን በቀላሉ የሚቀይር ነገር ነው፤ ለምሳሌ ወተት** ብለው ይንገሩት።
- የበረዶ ኩቡን እና ውሀውን አወዳድሩ። **ጠጣር የሆነው የትኛው ነው? አዎ፣ የበረዶ ኩቡ፤ የበረዶ ኩቡ የተጋገረ ውሀ ነው። እስኪ በረዶውን ወደ ፈሳሽነት መቀየር እንችል እንደሆነ እንይ** ብለው ይንገሩት።
- በረዶውን ሞቃት ቦታ ላይ አድርጉና ሲቀልጥ ተመልከቱ፤ ወይም በጥቂቱ ምድጃ ላይ ያድርጉት ወይም በሞቃት እጅዎ ይያዙት። በረዶው ሲቀልጥ ልጅዎን ምን እንደሚታየው ይጠይቁት።
- *በአማራጭነት - በጠጣር ነገሮች እና ፈሳሾች ላይ ምርምር ማድረግ የሚቻልባቸው የተለያዩ አዝናኝ ዘዴዎች አሉ! በከረጢት ወይም ድስት ውስጨጥ በማድረግ ቀላል አይስ ክሬም ይስሩ ወይም ጭማቂውን ፖፕሲክሎች ለመስራት ያቀዝቅዙት*

## በግል መማር፦ የሚረጭ ውሀ ስዕል

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፦ ውሀ፣ ውሀማ ቀለም ጥቅል፣ ወረቀት፣ የቦታ መከላከያ ጋዜጣ፣ *በአማራጭነት - ሌሎች የማስዋቢያ ቁሶች፤ ምሳ: የዝናብ ጠብታዎችን የሚሰሩ ደመናዎች ማስመሰያ የጥጥ ኳሶች***

- ለልጅዎ **እስኪ ውሀና ቀለም በመጠቀም የሚረጭ ውሀ አርት እንስራ!** ብለው ይንገሩት
- ልጅዎን የውሀ ቀለም እንዲሰጥ ውሀው ላይ ቀለሙን እንዲጨምር ይርዱት። ቅይጥ ቀለም በመጠቀም ሙከራ የመስራት ምሳሌ ሊሰጡት ወይም ልጅዎን እንዲመራመር ሊፈቅዱለት ይችላሉ። የቀለም መቀቢያ ቡርሽ በመጠቀም፣ ቀለሙን በመበጥበጥ፣ ቀለሙን ወደ ኋላና ወደፊት በመውሰድ፣ የዝናብ ጠብታዎችን በመስራት፣ ወዘተ የተለያዩ አይነት ርጭቶችን ለመስራት ሞክሩ።
- ለልጅዎ የራሱን የመረጨት አርት እንዲሰራ ይፍቀዱለት።
- ከዚያም **አርትህን ለመስራት ቀለሙን እና የመቀቢያ ቡርሹን የተጠቀምከው እንዴት ነው?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 9 ሳምንት 2 ቀን 9

## እውቀት፥ ችግር እና መፍትሄ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** Four Problems Part 1/ የአራት ችግሮች ክፍል 1, **ከለሮች**




- ለልጅዎ **ችግር ማለት የሆነ ነገር ሲሳሳት ነው። መፍትሄ ደግሞ ችግሩን የመፍቻ ዘዴ ነው** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም **እስኪ እነዚህን ችግሮች እንያቸውና መፍትሄ እንፈልግላቸው** ይበሉት። ለልጅዎ እየወደቀ ስላለ ከብሎኬት የተሰራ ማማ ስዕል ያሳዩት። ከዚያም **ችግሩ ምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት። መፍትሄውንም እንዲያስብ ይጠይቁት። በጋራ ሆናችሁ ሊሰሩ ስለሚችሉ መፍትሄዎች ተነጋገሩ። የታመመ ሰው ስዕል በመጠቀም ሙከራውን ደግማችሁ ስሩ።
- ልጅዎን ስዕሎቹን ቀለም እንዲቀባቸው ይፍቀዱለት።

## የጆርናል ሙከራ፥ የውሀ ቁጠባ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ እርሳስ፣ የውሀ ቁጠባ የጆርናል ገጽ**




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ውሀ መቆጠብ ስለሚቻልባቸው ስለተለያዩ ዘዴዎች ተነጋገሩ፤ ምሳ፡ ጥርሳችንን በምንቦርሽበት ወይም እጃችንን በምንታጠብበት ወቅት ቧንቧ መዝጋት።
- ልጅዎን ስለዚህ እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ከዚያም **ውሀ መቆጠብ የምንችልበት ዘዴ ምንድን ነው? እስኪ ይህን በቤት ውስጥ እንሞክር!** ብለው ይጠይቁት።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



የብሎክ ህንጻው ተደረመሰ



ህመም እየተሰማው ነው


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ _________________

ውሃን ስለምንቆጥብበት ወይም ስለምንጠብቅበት አንድ መንገድ ስዕል ሳሉ እና ጽሁፍ ጻፉ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ



## **STEM:** የዝናብ ጠብታዎች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፦** [Raindrop Sets/የዝናብ ጠብታዎች](), **ከለሮች, ደህንነቱ ለልጆች የማያሰጋ መቀስ**



- ለልጅዎ **በዚህ ገጽ ላይ ምን ያክል የዝናብ ጠብታዎች እንዳሉ ቁጠር** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም **አሁን የዝናብ ጠብታዎቹን ቀለም መቀባትና ቆርጠህ ማውጣት ትችላለህ** ይበሉት። አስፈላጊ ከሆነ ልጅዎን ቆርጦ በማውጣት ላይ ይርዱት።
- ከዚያም የተለያየ መጠን ያላቸው የዝናብ ጠብታዎች ያስቀምጡ፤ ለምሳሌ፦ 1 የዝናብ ጠብታ፣ ከዚያም 5 የዝናብ ጠብታዎች፤ ከዚያም ልጅዎን የዝናብ ጠብታዎቹን እንዲቆጥራቸው ይጠይቁት። ልጅዎን በጠቅላላው ስንት የዝናብ ጠብታዎች እንዳሉ ይጠይቁት። ጠብታዎቹን ከቆጠራቸው መጨረሻ ላይ የሚጠራው ቁጥር ድምራቸው እንደሆነ እንዲረዳ ድምራቸውን ይንገሩት። **1፣ 2፣ 3፤ በጠቅላላው 3 የዝናብ ጠብታዎች አሉ** ይበሉት።

## በግል መማር፦ የመቀነስ፣ ድጋሚ የመጠቀም፣ መልሶ የመጠቀም ፖስተር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፦ ወረቀት፣ ውሀማ ቀለም ጥቅል ወይም ከለሮች**

- ከልጅዎ ጋር የቆሻሻ መጠንን ለመቀነስ የሚጣሉ ነገሮችን መቀነስ (ምሳ፡ ለጽዳት ጥቂት ሶፍት መጠቀም)፣ ድጋሚ መጠቀም (ምሳ፡ ከወረቀት አንደኛው ጎን ይልቅ ሁለቱንም ጎኖች መጠቀም) ወይም መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል (ምሳ፡ ጠርሙሶችና ድስቶች) ስለሚቻልባቸው ዘዴዎች ተነጋገሩ።
- ከዚያም **እስኪ ሌሎች ሰዎችን እንዴት መቀነስ፣ ድጋሚ መጠቀምና መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚቻል ለማስተማር ፖስተር እንስራ** ብለው ይንገሩት። ልጅዎን የራሱን ፖስተር እንዲሰራ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **እስኪ ስለ ፖስተርህ ንገረኝ!** ብለው ይጠይቁት። ለልጅዎ ፖስተሩን የት እንደሚያስቀምጥ እንዲወስን ይፍቀዱለት። በተጨማሪም ለጓደኞቹ ወይም የቤተሰብ አባላት የሚያሳያቸውን ምስሎች ልትወስዱ ትችላላችሁ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ



## እውቀት፥ ታሪኬ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለሮች**

- ልጅዎን **እስኪ በዚህ ሳምንት ስለተከሰተ ስለሆነ ነገር የተመለከተ ታሪክ እንጻፍ። ስለተከሰቱብህ ስለ ሁለት ነገሮች ልታስታውስ ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት። ከልጅዎ ጋር በታሪኩ ውስጥ ማካተት ስለሚችላቸው ስለ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ነገሮች ተነጋገሩ። ልጅዎን ታሪኩን እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ታሪክህ ንገረኝ! ታሪኩን ልትትተውነው ትችላለህ** ብለው ይንገሩት

## ያንብቡ፥ ***Trash/ትራሽ!***

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [*Trash/ትራሽ!*]

- መጽሀፉን ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆናችሁ አንብቡ።
- ከዚያም እንደ ቆሻሻ ከመጣል ይልቅ መልሳችሁ መጠቀም ስለምትችሏቸው ቁሶች ተነጋገሩ፤ ለምሳሌ፡ ጠርሙሶች እና ሳጥኖች።
- ሳምንቱን በሙሉ ለልጅዎ መልሳችሁ የምትጠቀሟቸውን ነገሮች በመለየት ላይ እንዲረዳዎ ይፍቀዱለት።

ትራሽ!




ደራሲ፥ በኬቲ አሌክሳንደር
ሰዓሊ፥ በአሌክስ ሳቭቹክ


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሳምንት 3


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ከእርሻ ማሳ ወደምግብ ጠረጴዛ

## በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥

በዚህ ሳምንት ልጅዎ፡ ከ5-8 ያሉ ቁጥሮችን ለይቶ ያውቃል፣ ጥምር ቃላትን ይፈጥራል፣ ስለእጽዋትና ውስጣዊ የመሬት ክፍል ይማራል። እነዚህን ተግባራት የእጽዋት ዘሮችን አብረው በመትከልና ሲያድጉም ክትትል በማድረግ ማስፋት ይችላሉ።



## ቁልፍ ቃላት



### ምድር

የምንኖርባት ፕላኔት



### ተክል

ህይወት ያለው ነገር እና በምድር ላይ የሚበቅል፣ ግንድ፣ ቅጠል እና ስር ያለው ነገር


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት ስለመሬት ውስጣዊ ክፍል ትማራለህ። ይህን የትምህርት ጥቅል መማር ከመጀመርህ በፊት የመሬት ውስጣዊ ክፍል ምን ሊሆን ይችላል ብለህ የምታስበውን በጽሁፍና በስዕል ግለጽ።

ያስቡበት!


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## **STEM:** ከ5-8 ያሉ ቁጥሮች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ በትንሽ ወረቀት ላይ ከ5-8 ያሉ ቁጥሮችን ይጻፉ፣ እያንዳንዱን ቁጥር በ2 የካርድ ቁጥሮች ይጻፉ።**

- እያንዱን ቁጥር ለልጅዎ በማሳየት ስማቸውን እንዲጠራ ያድርጉ። እርዳታ የሚፈልግ ከሆነም እርስዎ ቁጥሩን እየጠሩለት ደጋግሞ እንዲጠራቸው ያድርጉ፣ ልጅዎም በጣቱ እንዲያመለክት ያድርጉ።
- ለልጅዎ አንድ የካርድ ስብስብ ይስጡና አንዱን ደግሞ ለራስዎ ይያዙት። **አንድ ጨዋታ እንጫወት! አንድ የካርድ ቁጥር አሳይሃለሁ። የቁጥሩን ስም እየነገርከኝ በእጅህ ላይ ካሉት የቁጥር ካርዶች ውስት የጠራኸውን አሳየኝ ብለው ይንገሩት።**
- ትዕዛዝ የረስጡት፡ ልጅዎ የካርድ ቁጥር እንዲያሳይ ያድርጉና ቁጥሩን እርስዎ ፈልገው ያሳዩት።
- የበለጠ ልጅዎን ለመፈተን ተጨማሪ ቁጥሮችን በመጨመር ወይም ከካርድ ቁጥሮቹ ጋር ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸውን ቁሶች እንዲያዛምድ ልጅዎብ ይጠይቁ።
- የካርዱ ቁጥሮቹን ለሚቀጥሉት ሁለት ወራት ተመሳሳይ ተግባራትን ለማከናወን ያስቀምጧቸው።

## በግል መማር፥ የአትክልት ስፍራን በስዕል መግለጽ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [Garden Scene/ጋርደን ሲን](), **የቀለም ዉሃ መደባለቂያ ዝርግ ሳህን ወይም ከለሮች**



- በአትክልት ስፍራዎች ውስጥ ሊገኙ ስለሚችሉ እንደ ተክሎች፣ አበባዎች፣እጽዋትና አትክለቶች ላይ ከልጅዎ ጋር ይወያዩ።
- ከዚህም በኋላ **እንዚህን የአትክልት ስፍዎች መሳል ትችላለህ ብለው ይንገሩት።** የራሳቸውንም የአትክልት ስፍራ መሳል ይችላሉ።
- ከዚህም በኋላም፡ **የአትክልት ስፍራ ቢኖርህ ምን ምን ልታሳድግበት ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## እውቀት፥ ቅላጼ መፍጠር እችላለሁ!

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Trash/ትራሽ!*

- መጨረሻቸው ላይ ተመሳሳይ ፊደል ያላቸውን ቃላት ለመጥራት ማድመጡን በደንብ ይተግብሩ ወይም ይለማመዱ። መጨረሻቸው ላይ ተመሳሳይ ፊደል ያላቸውን ቃላትን እንደ ሆፕ፣ ፖፕ ያሉትን ጥራ- እኔ እያነበብኩልህ መጨረሻቸው ላይ ተመሳሳይ ፊደል ያላቸውን ፊደሎች አዳምጥና ለይ ብለው ይንገሩት።
